# የማረሻ ድክመት የማረሻ ነገር

ከገበሬው አስቻለው

ከእንግዲህ ጌቶቹን አፈር አይንካቸው
ማረሻው ዶዱሞ ቀለብ ከነሳቸው
አቡን እንዳልለው ቅስና የለው
ነጋዴ እንዳልለው ወረትም የለው
ሼህም እንዳልለው ሲሰግድ አላየው
ገበሬ እንዳልለው ማረሻ የለው
ይህን ሰው ከንግዲህ ምስጥር ከልክለው
ማረሻው ጎልድፎ ሰርዶ አልነቅል ሲል
ቃላት አላገኝም ዝምብዬ ልሳል
ጌቶቹ ከእንግዲህ አፈር አይንካቸው
በርበሬው  ቀላና ከዳር አወጧቸው
ሰፌዱም ያበጥር ወንፊት ይነፋበት
ሳደን ለመስፈሪያ
አብሮ ይጓዝ ነበር ይህ ሁሉ ማፈሪያ
ወንፊትም ይለያል ሽርክትና ልም
እንግዲህ ለአቡኑ ምስጢር አልሰጥም
አቡኑ ከእንግዲህ መስቀሉን ቢተውት ወይ ባማረባቸው
ሁልጊዜም መሳቂያ መሳለቂያ ናቸው
ፀሃይም ብትለግም ብትነሳን ብርሃን
እንተያያለን ደመናም ቢሆን
ዝናም ከዘነበም ጥላም አያሻን
ታዬን ከርቀቱ ድምፅ እንኳ ሳንሰማ
ከውስጥ ነው ሚጀምር እንቁላል ሲገማ
ማረሻው ቢደዱም አፈር ባያወጣ ሰርዶ ባይነቅል
ቆፍሮ ማየት ነው ቀለቡን ቢትል
ተቆፍሯል ብለን ስናለሰልሰው
ተመሳሳይ አጣሁ እኔማ ለዚህ ሰው
እነዚያ ሲሄዱ እነዚህ ሲከዱ
ሁሉም ያስሄዳል ሰፌ ነው መንገዱ
ዓርብ ቀን ስቅለት ነው ከትንሳኤ በፊት ወይም ከፋሲካ
ጥለውን ከሮጡ ጨለማው ሳይነጋ
ብዙ ጉድ አሳየን የዘንድሮው በጋ
ወንጀል በፍትሐብሔር ተጠግቶ አይድንም
ስንሰማ ዋልነና ያንንም ይህንም
ለፍርድ ስንዘጋጅ ጌቶቹ ግን የሉም
ውሽባ ገብቶ ነበር ማረሻውም ታሞ
ሰውም እንዳይሰማ አስታማሚ ደግሞ

እርሱም በሽተኛ በቁሙ የተኛ
እርሱም ውሸባ ገባ እንደማረሻው
ከእንግዲህ ዘለቄ ምህረቱን ይሰጠው
ዛሬ የለም እንጅ ምስጢሩ ቢኖር
ስንት ጉድ ስንት ጉድ ስንት ጉድ ነበረ
ከምስጢሩ ጋር አብሮ ተቀበረ
ያን መሳይ አዛውንት በእድሜው የከበረ
ይህንን ይሰራል ማን ብሎ ነበረ
አበበ አይነኩሉን ሳናውቀው ቁርጡን
አፈዴበት አሉን የማይሆነውን
ፀሎቱን አክለን ፀጋ ቢሆነን
በረከት እንዲወርድ እንዲሳካልን
መርገሙ ይሻላል እንዳንኮነን
እንዲህ ያለ ምስጢር ከወዴት ተገኘ
ለወገን ነፃነት እራሱን ያሞኘ
ማረሻ እንዲህ ሆኖ ሰው ከሚአዝንበት
ይሻለው ነበረ ጋሻላ መግባት
በልምራኝ እያልሁት ሲከዳኝ ከአደረ - አታግለኝ እያልሁት ሲሽጠኝ ከዋለ
ከዚያበልጠ ወያኔስ ምን አለ ፥ ከዚህ የበልጠ መለሰ ምን አለ?